# አቧራው ጨሰ!! በስቶክሆልም ባንዳዎች አንገታቸውን ቀና አደረጉ!!

በሃገራችን ኢትዮጵያ በከፋ ፈታኝ ዘመን ላይ ወድቃለች:: ማንም ትውልድ በዚህ መልኩ ውጣ ውረድ አልኖረም:: የአገዛዙ የቅጥፈት ሰለባዎች ተበራክተዋል:: የወያኔ የዘር ፖለቲካ ስብዕናችንን እየሰረሰረ ከአንድ አገር የመጣን ሰዎች አንዳችን ስለሌላው መብትና ደህንነት እንዳንቆረቆር በሌላው ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረን አንዳች የሌላውን ንፁህ ህሊና በጥርጣሬ እንድናይ፣ የሌላውን ሳቅ መሳቅ የሌላውን ስቃይ መቁሰል በማንችልበት የጥላቻ እስር ቤት እንድንገባ ተደርገናል:: ፍለጠው፣ ቁረጠው፣ ግደለው፣ እሰረው፣ ዝረፈው የሚለውን ትዕዛዝ በሚያስተላልፉት ላይ በደሉ የሚደርስበት ዜጋ ይህን ክፉ ዘመን ለማለፍ ያችን ድል ዕለት እየጠበቀ እንደሆነ መገመት አያዳግትም:: በወያኔ ወታደሮች ቤቱ የተቃጠለው፣ የታረደው፣ መብቱን ወጣት ሴት ልጁን የተደፈረበት፣ መንደሩ የጋየው፣ የተፈናቀለው፣ በገፍ የተጋዘው፣ የተዋረደው የተዘረፈው የዘር ማጥፋት እርምጃ የተወሰደበት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጭቱን ይዞ ለፍትሃዊ ስርዐት መመስረት ቆርጦ ተነስቶቷል:: በዲያስፖራውም ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ለወገኑ መጐሳቆልና መገፋት ከፍቶታል::

በወያኔ ዘመን የሰርአቱን ዝቅጠት የሚተቹ ለሰብአዊ ህልውናቸው እውቅና የማትሰጥ እየለቀመች የምታስር፣ የምትገል አገር ሆናለች:: ካድሬና ባንዳ፣ ሌባው፣ ነፍሰ ገዳዩ ሙሉ ሰዎች ሆነው የሚታዩበት አገር ሆናለች:: የዚህ ዘመን ዘመነኞች ባንዳዎች እንደሚሉት ሳይሆን ኢትዮጵያ ቀድሞ ከነበረችበት በእጅጉ የኋሊት ተጉዛ ለዜጐች የማትመች ገሃነም በልቶ ማደር ብርቅ የሆነባት አለያም በልቶ ለማደር ህሊና በማስያዥነት የሚቀርብበት የሲኦል መዲና ሆናለች::

ባለፉት 24 ዓመቶች ከአንዳንድ ብሔረሰብ የተለቃቀሙ ትናንሽ ግልገል ፋሽስቶች በስተቀር በዋነኝነት ወያኔዎች የሚያሰማሩት የሚያምኗቸውን የትግራይ ተወላጆችን ነው:: የወታደራዊና የሴኩሪቲ ተቋማት በሙሉ የሚቆጣጠሩት ወያኔዎች ናቸው:: ፍለጠው፣ ቁረጠው፣ ግደለው የሚለው ትዕዛዝ የሚሰጠው ከወያኔዎች ነው::

ወያኔዎችም የትአባክ ምን ትሆናለህ ሥልጣን በትግሬዎች እጅ ገብቷል ብለው ሳይሸማቀቁ ይደነፋሉ:: የስቶክሆልም ባንዶች ግን በጐረሱት ጥቅም ላይ ቆመው የ ethnic apartheid አገዛዝ የጥቂቶች ሳይሆን የሁላችንም ነው፣ የልማት መንግስት በመሆኑ አትቃወሙብን ይላሉ:: የአገር ናፍቆት፣ የአንድነት ታሪካችን ባለቤትነት ክፍተት፣ የጀግና መጥፋት፣ የትውልድ መዋለል፣ ከፍተኛ ብሔራዊ ውድቀት ወደ አለየ አቅጣጫ እየወሰደን ነው:: በቁሙ የሞተ፣ ሞቶ ያልተቀበረ የታሪክ ቅብብል የሚከድ ትውልድ በመበርከቱ ባንዳዎች በቀረችን ዕድሜ ክህደት ልብሳችን ይሁን ብለው ፈቅደው በወያኔ ኤምባሲ ውስጥ መሽገዋል::

የፀረ ዘረኝነት የቤት ስራችንን ስላልሰራን ለሕዝብ ደም የሰከሩ ወያኔዎች አሽቃባጮቻቸውን ወደ ሜዳው ለቋቸዋል:: በስዊድን በሌሎችም ከተሞች የርኩስ ዓላማ ዓዝማች እንሁን ያሉ በእሽቅድድም ላይ ናቸው:: ውርደት ጨርቃቸው በመሆኑ ያለፈ ታሪካቸውን መለስ ብለው አያዩም:: ከወያኔ በላይ ወያኔ ለመሆን እየጣሩ ነው::

ወያኔ በዲያስፖራው የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳውን የሚያስፋፋበትን ቀጥሯል:: ከጥቂት ወራቶች ወዲህ በስዊድን በቀሩትም አውሮፓ ከተሞች ባንዳዎች ተበራክተዋል:: የዘመኑ ባንዳዎች ከአንድ ጉድጓድ የተቀዱ ናቸው:: የጋራ ባህሪያቸው "በጥቅም ባርነት ስር ለመነዳት ፈቅዶ መገኘት ነው ":: ሌላው ከህሊና ጋር የታረቀ ኢትዮጵያዊ በጥቅም ባርነት ስር ካልተሰለፈ ስም ይለጠፍለታል:: የወያኔን

ዘረኝነት፣ ሙስና፣ ፀረ-ሕዝብ ፣ ፀረ-ሃገር ተግባሮች ይከዳሉ። ተቃዋሚዎችን በፈጠራ ወሬ አዋርዶ፣ ሰማይ ተሰበረ፣ ደደቢት ተራራ ተናደ እያላችሁ ውዥንብር አሰራጩ በዚህ ውለታችሁ ጥቅማችሁ እንዳይጓደል አደርጋለው በሚል ቃል ኪዳን ተሳስረው እየሰሩ ነው። ባንዳዎቹ በተለያዩ መንግሥታቶች የተለዋወጡ በመሆናቸው ክፉ ቀን ቢመጣ ይከዱኝ ይሆናል በሚል ስጋት በተቀዋሚዎች ላይ ፀያፍ ፕሮፓጋናዳ እንዲያካሂዱ ወያኔ ትዕዛዝ አስተላልፏል።

ዛሬ ወያኔ ሙብራት በሃገሪቷ ሲጠፋ ሻአቢያ አስቸግሮኝ ነው ይላል፣ ውሃ ከከተሞች ሲጠፋ ተቃዋሚዎች አደናብረውኝ ነው ይላል፣የስቶክሆልም ባንዳዎች ግን ሙብራትም ሆነ ውሃው በፈረቃ ሳይሆን ሙብራትም እንደ ጠራራ ፀሐይ ብርሃን ደምቋል፣ የውሃውም ቧንቧ ጠቦት ጐርፍ በጐርፍ ሆነናል እያሉ ነው። ውሸትና ሌብነት ሌላ መረጃ ይኖረው ይሆን? የባንዳዎች አባወራዎች በዚህና በሌላም ድርጊቶቻቸው ቢያንስ ጤነኛ አይምሮ ያለው ወገን፡ --ባንዳዎች--ሌቦች ይላቸዋል። ባንዳዎች ግን እርስ በርሳቸው የሚያወሩትን ተደማምጠው፣ ራሳቸውን አድምጠው አይ ሌባው ሌላ ነው ይላሉ። ወያኔ ጋር ሲጎራረሱ መካድንንም ያዋጣቸው በመሆኑ፣ ከወያኔ ጋር ብንውልም ባንዳዎች ልንሆን አንችልም የረቀቀና የመጠቀ ውይይት አድርገን ስልጡን ወያኔዎች ሆነናል ይላሉ።

የባንዳዎች አዝማች በቅርቡ በስቶክሆልም በወያኔ የፕሮፓጋንዳ ማሰራጫ ቀርቦ እንዳረጋገጠው በተለያዩ ጊዜያቶች አምባሳደሮች ጋር ሲመካከር እንደነበር እራሱን አጋልጧል። በሰጠው ቃለመጠይቅ በስዊድን የወያኔ አምባሳደር የነበረ በአሁኑ ወቅት በለንደን የወያኔ ሹም ጋር ባደረጋቸው መቀራረብ ቤት አዲስ አበባ ለምን አትሰራም ብሎ መክሮኝ ነበር ብሏል። የባንዶች አዝማች ይህን እሱ የሚለውን ግንኙነት የፈጠረው ከ8 ዓመትች በፊት ሲሆን በዚያን ወቅት በተቃዋሚነት ውስጥ ሆኖ የስለላ ተግባር እንዳካሄደ ጉልህ ማስረጃ ሆኖ ወጥቷል። እነዚህ ናቸው ክብር ከገቢያ ሊሸምቱ የሚፈልጉ፣ መጥፎ ባህሪያቸውን መግለፅ ዋጋ ያሰጣል ብለው በአደባባይ ማንነታቸውን የሚነግሩን። በሰውር የሚያከናውኑትን ፈጣሪ ይቁጠረው።

የወያኔ ባለሟሎች ሰሞኑን አንድ ባለሰባት ገፅ ፅሑፍ ለወዳጆቻቸው በትነዋል። ውሸትን የመሰለ ጨካኝ ነገር የለም። በተለይ የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ተማራኪ የሆነ አፍ ሲያወጣው የባንዳነት ማረጋገጫ ባህሪያት ለመሆኑ ግልፅ ሆኖ ይታያል። ሰዎቹ ይሉኝታ ስለሌላቸው "ባንዳ" ለግንቦት 7 የአዞ እንባ ለማፍሰስ እንደሚዳዳው በፅሁፋቸው ነገሩን። ወይ የባንዳ ዘመን ወያኔም መሆን ግንቦት 7 ም መሆን አንድ ነው እያላችሁ ይሆን እንዴ? ታድያ ለምን በግንቦት 7፣ በእሳት ድግስ ለመታየት አልሞከራችሁም? ወይንስ ግብረገብነት አጥታችሁ ላደጋችሁበት ባህሪ ሁለት ባላ ላይ መንጠልጠል አማራችሁ? ነውር የሚባል ነገር በውስጣችሁ የለም። ይህንን የእናንተ አእምሮ ብቻ ነው የሚያስተናግደው።

ወደተበተነው ፅሑፍ እንመለስና ለተቃዋሚዎች መወቀስ አዝነናልና የአዞ እያነባን እንንቀፋቹህ በሚል መንደርደሪያውን ያደረገ ፅሑፍ ይሁንብን ብለው ግለሰቦችን ጥላሸት በመቀባት ርካሽ ማንነታቸውን ካጋለጡ በኋላ መደምደሚያውን ወያኔን አሞካሽተውና አሳምረው ለተላኩበት ተግባር ታማኝነታቸውን ገልፀውበታል:: ለተበተነው ፅሑፍ ተጠያቂዎች የምንላቸውን እንጠቅሳለን፣

1. ታደሠ ኰስትሬ
2. አብረሃም አገኘሁ
3. መሠረት መንግሥቱ
4. ጌታቸው ዋና

## 5. ዘውግ ተክሌ
## 6. በላቸው መንገሻ

መሆናቸውን አንባቢው እንዲረዳ እንፈልጋለን። ከነዚህ ሰዎች ጋር ስማቸውን በዚህ ፅሑፍ ያልጠቀስናቸው የወያኔን ውለታ ለመክፈል የሚራወጡትና የአገር ሐብት ለማውደም በወያኔ ጫማ ስር ያሉም ስላሉ ጊዜውን ጠብቆ ተከታይ መልክት ይሰጥበታል።

ባንዳዎች ሰርቶ በማደርና ከነፍስ በላው አገዛዝ ተሻርኮ የሃገር ሐብትን ማውደም መካከል ያለውን ልዩነት ለመረዳት አእምሮዋቸው አይታዘዝላቸውም። ሰው ሰርቶ በላቡ ያገኘውን በፈለገበት ቦታ ቢያውለው ሃጢያት ወንጀልም አይደለም። የሃጢያት ሃጢያት፣ የከፋው ወንጀል በተጭበረበረ ሁኔታ የሃገር ሃብት ለመዝረፍ ከወያኔ ጋር ተባብሮ መገኘት ነው። በራስ ጉልበት የተገኘ ገንዘብ ጠጡበት የሚለውን ነውር መሆኑን ከነገራችሁን እኛስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ደም መምጠጥ አስነዋሪነት በምን ቋንቋ እንንገራችሁ። እውነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ማን በስቶክሆልም ጠጣ ብሎ ያስባል ብላችሁ ይሆን ? የሚያስበውንና  ለፍርድ የቸኰለበትን  እንንገራችሁ - ማን ደሜን መጠጠኝ - በምንስ መልክ ልካስ ነው የሚለው። ለወዳጆቻቸው የበተኑት ፅሑፍ አንዱን ከአንዱ አጣልተው ዋሽተን፣ አጣልተን እርኩስ ዓላማችን ይሳካል በሚል ወያኔያዊ መንፈስ የተለቀለቀ ነው። ራሳቸውን በሰው ፊት ከፍ ያደረጉ መስሏቸው የግለሰቦችን አኗኗር እናውቃለን ሰካራም፣ ጠጪ ብላችው ከአላማቸው እንዲያፈገፍጉ እናደርጋቸዋለን ብለው በወጠኑበት ሴራ ብዙ ብለዋል።

ሰዎች ያላቸውን በጐ መንፈስ ለአገር ፍቅር እና ለአገር ክብር የሰጡ፣ ለገንዘባቸው ሳይሳሱ ምቾትን ርቀው በእውነት ጐዳና ከተጓዙ ባንዳዎችን እንደትቢያ መመልከት ይቻላል። የሰው ልጅ በእውነት ጐዳና ለእውነት ቆሞ ውስጣዊ ህሊናውን ካነፀ ከራሱ ህሊና ውጭ ምንም ነገር ሊያስበረግገው አይችልም። ለሰው ልጅ ውስጣዊ የህሊና ንፁህነቱን ማንነቱ ማረጋገጫው እውነትን ገንዘብ ሲያደርግ ብቻ ነው። ታላቅነቱ የሚለካው ከሌብነት መራቅ ሲችል ነው። መንፈሱ የነፍሰ ገዳዮዎች እኩይ ተግባር ማደሪያ ካልሆነ ነው። በዚህ በንፁህ የሰው ልጅ ባህሪ የታነፀ ገድሉ ሲወራለት ይኖራል።

ውሸታም ሰው ግን ሐሰትን ተላምዶ መተዳደሪያው ካደረገ ከተራ ውሸታምነት ወደለየለት የአይምሮ በሽተኝነት (pathological liar) ለመቀየር ጊዜ አይወስድበትም። ምክንያቱም ራሱ የፈጠረውን ውሸት በልቡ ማመን ሲጀምርና በውስጡ የጐነጐነውን ሐሰት ሌላው ሰው እንደእርሱ እንዲያምነው ሲጥር ውሸት አሲድ ሆኖ  ውስጡን በልቶታል ማለት ነው። ባንዳዎች በዚህ ተርታ እንደቆሙ ፅሑፋቸውን ማንበቡ በቂ መረጃ ነው። በልብስ የተሸፈነው ሰውነታቸው የአውሬነት ባህሪ አለው። ብላችሁ ብላችሁ በስቶክሆልም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መድሃኒዓለም ቤተክርስቲያንንም ለርኩስ አላማችሁ ተጠቀማችሁበት። ምዕመናኑ የእነዚህን እርካሽ ሰዎች ቅጥፈት ማጋለጥ አለበት። ወያኔ መሆን በውሸት ጐዳና መገኘት ማለት ነው። ለመሆኑ የመድሃኒዓለም ቤተክርስቲያን ገንዘብ ተበላ ስትሉ እንደካህን ሆናችሁ ነው ወይንስ በአመራር ላይ የስራ ድርሻ ይዛችሁ? ፈሪሃ እግዚአብሄር በእናንተ ባህሪ የለም፣ ቤተክርስቲያኗ ማን መዋጮ እንደሚያደርግና ማን እንደማያደርግ ያወጣችው የስም ዝርዝር የለም። እንዴት መቼ ወደ ባንዳዎች እጅ ሊስቱ ተላለፈ?

በወያኔ ዘመን በዲያስፖራ ውስጥ ያሉ ባንዳዎች በገሃድ የሚታይና ከሕዝቡ የተሰወረ ወንጀል እየፈፀሙ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ መንፈስ ግን እያያቸው ነው። የስዊድን ባንዳዎች ሌብነትን ወያኔ በሰጣቸው ፈቃድ እያካሄዱ ነው። ዝርፊያው በጦፈበት መስክ አንዱ " money laundering" " penningtvätt "

እየተካሄደ እንደሆነ ብዙዎቹ ይመሰክራሉ። የአገር ሃብት ለማሸሽ የተባበሩ በሻንጣና በአገልግል ዶላር እያወጡ ናቸው። ወያኔ የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት "chronic " ሆኖብኛል እያለ ያማርራል። የራሱ ባንዳዎች ግን የገንዘብ ሽግግር፣ ልውውጥ እያደረጉ ነው። ይህን ወንጀል አስመልክቶ በስዊድን ያሉ ባንዳዎች መካከል የተወሰኑትን መጠቆም ይቻላል። ባንዳዎቹና የባንዳዎች ጌታ ወያኔ እርስበርስ ይተዋወቃሉ።

ዛሬ በሕዝብ መከራ የማታላግጥ ወገን ስማ!! ባንዳዎች ከብጤዎቻቸው ጋር ሆነው በዚህ አካባቢ ያለውን ተቃውሞ ዝም ለማስባል ተንሸራተው ገደል እየገቡ ነው፡ ለጊዜው ሰሚ አጥተዋል። አጋፋሪውና የባንዶች አባት የሆነው ታደሰ ኰስትሬ በየሰው ስልክ በመደወል የወያኔ ኢምባሲ ሁሉን ነገር ያቀርብልናልና ክስ እንመስርት እያለ ሲወተውት ሰንብቷል። ከዚህ ቀደም ሲል በሻርሆልመን ኩንግስ ኩርቫ በሚገኙ ሻይ ቤቶችና መጠጥ ቤቶች ከዚያም በግለሰቦችም ቤት በመሰብሰብ መንጋዎችን ለማጣመር ብዙ ለፍቷል። በግለሰቦች ቤት ስራው ሲቀነባበር ሰንብቷል። በነፃው ዓለም ወያኔ አላስታጠቃቸውም እንጂ ወያኔ/ትግሬ ተኩሱ ቢላቸው ዝግጁ ናቸው። "የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ" ሆኗል። ወያኔ በወያኔነቱ ሳያፍር ሕወሓት/ወያኔ በሉኝ እያላቸው ግልገል ባንዳ ፋሺስቶች ግን ባንተ አምነናልና ሌላውንም አስፈራርተን እኛ በምናይብህ አመለከካታችን እንዲያይህ እናደርጋለን በሚል የባንዳዎች ማኅበር በመመስረት ዛቻ እያካሄዱ ነው። በቁሳዊና በሥጋዊ ባርነት ስር ስላሉ ስብዕናቸው ነቅዟል።

Stockholm
2015-03-10